በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት
ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
አሶሳ

The Benishangul Gumuz Regional State
Bureau of Finance & Economic Development
Assosa

ቁጥር 3/9/05/44
Ref. No.
ቀን 12/02/421
Date

በአባሪዉ ለተዘረዘሩት መ/ቤቶች በሙሉ

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የተሻሻሉ የመንግስት ግዥ አፈፃፀምና ንብረት ማስወገድ

አንቀጾችን ስለመግለፅ

የቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 96/2003 ዋና ዋና ዓለማዎች የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ ግልፅ፣ ቀልጣፋ፣ፍትሐዊ እና አድሎዎ የሌለበት፣ እንዲሁም ዉጤታማ እና ለግዥ የሚዉለዉ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኙን ፋይዳ ማግኘት በሚያስችል መልኩ ሥራ ላይ እንዲዉል ማድረግ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ይሁን እንጂ ዘርፉ በባህሪዉ ተለዋዋጭ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በሀገር ሆነ በክልል ደረጃ እየታየ ያለዉ የብር የምንዛሪ ለዉጥ እና ተያያዥ የገበያ ሁኔታዎች በግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ተግባራት ብሎም በመንግስት መ/ቤቶች ዋና ዋና የልማት ግቦች ትግበራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን አፈፃፀም የበለጠ አመቺና ቀላል ለማድረግ፣ እንዲሁም ዉጤታማ እና ለመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኙን ፋይዳ በሚያስገኝ ሁኔታ ለመተግበር ይቻል ዘንድ ከዚህ በታች በተመለከቱ በአፈፃፀም ላይ በሚታዩ ዋና ዋና ችግሮች ዙሪያ የአሰራር ማሻሻያዎችን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት፤

1. **የግዥና ንብረት ገንዘብ ጣሪያን** /threshold/ **በተመለከተ** ላለፉት ዓመታት በአገር ደረጃ የተደረገዉን የብር ምንዛሪ ማሻሻያ ጋር በተያያዘ በገበያዉ ላይ የተፈጠረዉን የዋጋ ንረት፣ እንዲሁም በሀገር ደረጃ እየተስተወለ ያለዉን የዉጭ ምንዛሪ እጥረት በግዥ አፈፃፀሙ ላይ እያሳደረ ያለዉን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማስቀረት እና የሀገር ዉስጥ አቅራቢዎችን ለማበረታታት እንዲቻል አሁን ሥራ ላይ ባለዉ የግዥ ገንዘብ ጣሪያ ላይ ማሻሻያ እንደሚከተለዉ ተደርጓል፡፡

ማሳሰቢያ፡-መልሱን ሲጽፉልን የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ፡፡ ☎ 057 7750302 /750303
Note :- Please Quote our Ref.No. When Replying. (Fax) 0577 750164
✉ 41 Assosa, Ethiopia

.ል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት
.ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
አሶሳ

he Benishangul Gumuz Regional State
Bureau of Finance & Economic Development
Assosa

ቁጥር 219/05/121
Ref. No.
ቀን 12/021/121
Date

| የግዥ ዘዴ | የግዥ ዓይነት | ነባር/በሥራ ላይ ያለዉ የገንዘብ ጣሪያ በብር | የተሻሻለዉ የገንዘብ ጣሪያ በብር |
|---|---|---|---|
| የብሐራዊ ግልፅ ጨረታ | የግንባታ ሥራ ግዥ | 150,000,000.00 | 600,000,000.00 |
| | የዕቃ ግዥ | 50,000,000.00 | 200,000,000.00 |
| | የምክክር አገልግሎት | 7,500,000.00 | 30,000,000.00 |
| | ያለየምክክር አገልግሎት | 21,000,000.00 | 84,000,000.00 |
| ዉስን ጨረታ | የግንባታ ሥራ ግዥ | 6,000,000.00 | 15,000,000.00 |
| | የዕቃ ግዥ | 1,500,000.00 | 3,000,000.00 |
| | የምክክር አገልግሎት | 900,000.00 | 2,000,000.00 |
| | ያለየምክክር አገልግሎት | 1,200,000.00 | 2,500,000.00 |
| የዋጋ ማቅረቢያ | የግንባታ ሥራ ግዥ | 300,000.00 | 750,000.00 |
| | የዕቃ ግዥ | 100,000.00 | 250,000.00 |
| | የምክክር አገልግሎት | 100,000.00 | 200,000.00 |
| | ያለየምክክር አገልግሎት | 120,000.00 | 250,000.00 |
| ለጨረታ ማስታወቂያና የዉል መረጃ በድረ-ገፅ ለመጫን | የግንባታ ሥራ ግዥ | 20,000,000.00 | 20,000,000.00 |
| | የዕቃ ግዥ | 6,000,000.00 | 6,000,000.00 |
| | የምክክር አገልግሎት | 4,000,000.00 | 4,000,000.00 |
| | ያለየምክክር አገልግሎት | 2,000,000.00 | 2,000,000.00 |
| ጥቃቅን ግዥዎች | ለአንድ ጊዜ | 5000.00 | 10,000.00 |
| | በዓመት | 75,000.00 | 150,000.00 |
| የአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ | የምክር አገልግሎት | 50,000.00 | 200,000.00 |

2. የመንግስት ንብረት ሽያጭ የጨረታ ማስታወቂያ የገንዘብ ጣሪያን በተመለከተ

- የመንግስት ንብረት ሽያጭ የጨረታ ማስታወቂያን በጋዜጣ ለማዉጣት በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 27/2012 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 ፊደል ተራ ረ ሥር በተራ ቁጥር 2 ላይ የተቀመጠዉ የገንዘብ ጣሪያ ከብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ ብር) ወደ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ከፍ የተደረገ ሲሆን በየደረጃ የሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶች፣ የዞንና ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያዎችና ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤቶች የተለያዩ የማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም አካባቢያዊ ማስታወቂያ በማዉጣት በክልሉ ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 27/2012 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3 በተሰጠዉ ስልጣንና የገንዘብ ጣሪያ መሠረት የመንግስት ንብረት በሽያጭ ማስወገድ ይገባቸዋል፡፡
- የክልሉ መንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 27/2012 በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት እንዲወገዱለት ከየመ/ቤቶች የቀረቡለትን ንብረቶችን በማስወገድ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሪፖርት እንዲያደርግ፣

ማሳሰቢያ:-መልሱን ሲጽፉልን የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ:: ☎ 057 7750302 /750303
Note :- Please Quote our Ref.No. When Replying. (Fax) 0577 750164
✉ 41 Assosa, Ethiopia

ቤ/ል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት
ፊኮኖሚ ልማት ቢሮ
አሶሳ

The Benishangul Gumuz Regional State
Bureau of Finance & Economic Development
Assosa


ቁጥር 219/05/44
Ref. No.

ቀን 12/04/14
Date

3. የገበያ ዋጋ መረጃን በተመለከተ በጨረታ መክፈቻ ዕለት ያለ የመነሻ ዋጋ ከማዕከላዊ ስታስቲትክስ ኤጀንሲ ካልተገኘ፡-

- ✓ ከጨረታ መክፍቻ አንስቶ አሸናፊ ተጫራቾች ተለይቶ ዉል እስክፈረም ድረስ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ሆኖ ለጨረታ መክፈቻ ዕለት ቅርብ የሆነ የዋጋ መረጃ እንደመነሻ እንዲወሰድ፣ እንዲሁም
- ✓ የቀጣይ ዋጋ ማስተካከያን በተመለከተ የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ በሚገባዉ ጊዜ በገበያ ዋጋ (current price) የማይገኝ ከሆነ በቀጣይ የገበያ ዋጋ መረጃ በተገኘበት ጊዜ ያለን የዋጋ መረጃ በመጠቀም የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግ፤

4. የግንባታ የሥራ ክፍያ ጊዜን በተመለከተ

የመደበኛ የጨረታ ሰነዱ እና በመንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ የተቀመጡትን የክፍያ ቀናት መነሻ በማድረግ፣ እንዲሁም መ/ቤቶች ከአማካሪዉ መሃንዲስ የክፍያ ማረጋገጫ ከቀረበላቸዉ ጊዜ አንስቶ ለክፍያዉ የሚሆን በጀት ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለማግኘት የሚወስደዉን ጊዜ  ከግምት ዉስጥ በማስገባት ከተቋራጮች ለሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎች ክፍያ መፈፀሚያ ከፍተኛ ጊዜ ወደ 45 ቀናት ከፍ እንድል የተደረገ መሆኑን እየገለፅን፤ የመንግስት መ/ቤቶች ከላይ በተገለፀዉ ማሻሻያ መሠረት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሆኖ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አፈፃፀሙን እንዲከታተል አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

አቶ ዚያድ አብዱላሂ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ

ቀን 12/04/2014 ዓ/ም

ግልባጭ

ለፋይናንስ ዘርፍ ም/ቢሮ ኃላፊ

ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

በቢሮዉ


ማሳሰቢያ:-መልሱን ሲጽፉልን የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ።   ☎ 057 7750302 /750303
Note :- Please Quote our Ref.No. When Replying.   (Fax) 0577 750164
✉ 41 Assosa, Ethiopia